# ዓለምለኸ ማሕበር ዴሞክራሲያዊያን ተጋሩ

# አለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር.

# International Tigrean Democratic Association

itda2005@yahoo.com

## ከዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር የተሰጠ መግለጫ

### ኢትዮጵያን ካልገዛናት እንበትናታለን

አቶ ስብሓት በ"ድምፂ ወያነ ትግራይ" በግንቦት 23፣ 24፣ 25ና 26 ቀን 1999 በትግርኛ፣ Ethiopians forum for political civility (የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ጨዋነት መድረክ) በሚባል ፕሮግራም ደግሞ ዓይጋ ድረገፅ ላይ የተደመጠው በአማርኛ በተላለፉት ቃለ ምልልሶቻቸው የድርጅታቸው አቋምና ታሪክ ነክ አስተያየቶች ገልፀዋል፡፡

አቶ ስብሓት ከሰጧቸው አስተያየቶች እውነትነት ያላቸውንና ከእውነት የራቁትን ለመለያየት፣ እንደዚሁም እውነት የሆኑትም ከህዝብ አንድነትና ከዴሞክራሲ አንፃር ሲታዩ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ያላቸውንና ጎጂ የሆኑትን ለመግለፅ ከህወሓት ታሪክ ጋር እያገናዘብን እናያቸዋለን፡፡

ህወሓት በተሓህት ስም በየካቲት 11 ቀን 1967 ዓ/ም ከተመሰረተ በኋላ አቶ ስብሓትና አቶ መለስ ከ1968 ዓ/ም ጀምረው ያመራር ቁልፍ ቦታዎች የያዙና የድርጅቱን አቋሞች በበላይነትና በብቸኝነት የሚወስኑ ግለ ሰቦች ናቸው፡ የሁለቱ ዋናው ትግልና ድልም ድርጅቱን በመቆጣጠር ላይ ነው፡፡ ሰዎቹ ከ30 ዓመታት በላይ ብዙ ግፎች እየፈፀሙ ስለቆዩ የስልጣን ተገን ሳይኖራቸው ባደጉበት መንደርም በሰላም መኖር የሚችሉበት ሁኔታ ያለ አይመስልም፡፡ ድርጅቱ ከሁለቱ ግለ ሰቦች በላይ ለትግሉ የላቀ አስተዋፅኦ ያደረጉ ብዙ ታጋዮች ቢያፈራም ሁለቱ ለቡድናቸው መሳሪያ የሚሆኑ ሰዎችን በመቀያየርና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች የሚያነሱትንና የነሱ መሳሪያ ያልሆኑትን ቀድመው በመቅጨት ወይም በማባረር ጅርጅቱን ሊቆጣጠሩ ችለዋል፡፡

አቶ መለስ በ1975 አካባቢ ላይ መጀመሪያ በተዘዋዋሪ መንገድ ስልጣን በአቶ አባይ እጅ እንዲጠቃለል አድርገው አቶ አባይን በማሽከርከር፣ በ1977 ማሌሊትን ከመሰረቱ በኋላ ደግሞ ቀስ በቀስ በይፋ በህወሓት ውስጥ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን

ከመያዛቸው በፊት በፈፀሟቸው ወንጀሎች እንዳይጋለጡ፣ ስልጣን እንዳያጡና ቅጣት እንዳይደርስባቸው አቶ ስብሓት ይከላከሉላቸው ነበር፡፡

አቶ መለስና አቶ ስብሓት መጀመሪያ ላይ ሙሉ ስልጣንና ውክልና ሳይኖራቸው መስራች አባሎችን (ካሕሳይ በርሀ፣ አስፍሃ ሓጐስ ወዘተ..) ብቻ ሳይሆን ባመራር ላይ የነበሩትንም (አረጋዊ በርሀ) ጭምር በማግለል በድርጅቱ ስም የድርጅቱ አቋም፣ ለምሳሌ ድርጅቱ የትግራይ ዴሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ለመመስረት እንደሚታገልና ለኤርትራ ነፃነት እንደቆመ መግለጫ ስላወጡ ባንድ በኩል በፀረ ደሞክራሲ አሰራራቸው ምክንያት ስልጣን እያለቸው ከተገለሉ አባሎች ተቃውሞ ሲያጋጥማቸው በሌላ በኩል ሻዕቢያ የትግራይ ነፃነት የሚለውን ዓላማ እንዲፍቁ ከፍተኛ ጫና አድርጎባቸው ነበር፡፡ (የሻዕቢያ ተቃውሞ ለኢትዮጵያ አንድነት ከመቆርቆር የተነሳ ሊሆን እንደማይችልና የኤርትራ ጥያቄ ልዩ ሆኖ መታየቱ ቀርቶ ከብዙዎች አንድ እንዳይሆንበት ስለሰጋ እንደነበረ መገመት አያዳግትም፡፡)

እነ አቶ መለስ የወጣው መግለጫ በእነማን እንደተፃፈ እንዳይገለፅ ጥፋታቸው በአባሎች እንዳይታወቅና ጥፋቱ የሁሉም ያመራር አባሎች መስሎ እንዲግበሰበስ አደረጉ፡፡ የውስጥ ተቃወሚዎቻቸውም በዚህ የተንኮል ወጥመድ ገብተው ጥፋቱን ለአባሎች ሳይገልፁ ከአስር ዓመቶች በላይ አቃጠሉ፤ እነ መለስ ግን ጊዜው ለሌላ ተንኮል ተጠቀሙበት፡፡

በዚህ መሰረት፣ እነ አቶ መለስ ዓላማቸውን ለማሳካት ፍፁም ስልጣን እንደሚያስፈልጋቸው ስለተገነዘቡ በድርጅቱ ውስጥ ቀስ በቀስ ስልጣን ለማጠቃለል ስልት ቀየሱ፡፡ ለዚህም የመጀመሪያው እርምጃቸው የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎችና ከዛ ውጭ የሆኑትን ታጋዮች መለያየትና በተራ አባሎች ላይ ሽብር መፍጠር ነበር፡፡ የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች በተራ ታጋይ አባሎች ላይ ያላቸውን የበላይነት ለማረጋገጥ፣ እነ አቶ መለስ በ1970 ድርጅቱን የሚያፈርስ የአንጃ እንቅስቃሴ ("ሕንፍሽፍሽ" ያሉት) የነበረ አስመስለው ቀሰቀሱ፡፡ ስልጣን የነበራቸው ሰዎች በፈፀሟቸው ስህተቶች ምክንያት ቅሬታቸውን የገለፁ ታጋዮች ባመራሩ ላይ እምነት እንዲጠፋ በማድረግ ድርጅቱን ለማፍረስ እንደሚንቀሳቀሱ ተወንጅለው ዘመቻ ተደረገባቸው፡፡

ቅሬታዎችን በማጣራት ፈንታ ቅሬታ እንዳላቸው የገለፁትን ለመመንጠር በተካሄደው ዘመቻ በድርጅቱ ውስጥ ሽብር ሰፈነ፡፡ የተውሰኑ ታጋዮች ድርጅቱን ጥለው በማምለጥ ህይወታቸውን አተረፉ፤ ከተያዙት የተገደሉም ታስረው የተሰቃዩም አሉ፡፡ ለምንጠራው የተመደበው ቡድን በ1971 ዓ/ም ለተካሄደው የድርጅቱ ጉባኤ ከተመረጡት የምርጫ ኮሚቴ አባሎች የቆመ አካል ነበር፡፡ ከዚያ ኮሚቴ አባሎች ውስጥ አንዱ (አባዲ ጎልያድ) የሽብር ድርጊቱን በመቃወሙ ሕይወቱ ሲቀጭ፣ አንድ ሌላ (ተሾመ ጉዶ) ከድርጅቱ አምልጦ በስደት ላይ ይገኛል፡፡ በዛ ፀረ ዴሞክራሲ ድርጊት አገልግሎታቸው ምክንያት ለሹመት የበቁ አሁን ቆይተው በነመለስ "አፈንጋጭ" ከሚባሉትም ነበሩ፡፡

ያ የሽብር ዘመቻ ካስከተለው የግድያ፣ የእስር ቤት ሰቆቃና ሽሽት በላይ የታጋዮቹን የዴሞክራሲ መንፈስ ስለገደለ ጅርጅቱን የጥቂት ፀረ ኢትዮጵያ ካሃዲዎችና

አረመኔያዊ አምባገነኖች መሳሪያ አድርጎታል፡፡ እነ አቶ መለስ ራሳቸው ባደረጉትና ለካድሬዎቻቸው ባሳወቁት ግምገማ ከዘመቻው በኋላ የድርጅቱ አባሎች እንደደነዘዙ (passive እንደሆኑ) ያምናሉ፡፡ ከዛ ወዲህ የህወሓት ታጋዮች ትእዛዝ ከመፈፀም ውጭ ባመራሩ ላይ ምክንያታዊ (reasonable) የሆነ ተቃውሞና ሂስ ማቅረብ፣ በካደሬዎች ከሚነገራቸው ውጭ መወያየትና ሃሳብ ማፍለቅ አቁመዋል፡፡ ስለዚህም የህወሓት አባሎች የፖለቲካ ሕይወት የላቸውም፡፡ በዚህ መሰረት ድርጅቱ የአቶ መለስና አቶ ስብሓት ፍላጎት ማስፈፀሚያ መሳሪያ እንደሆነ አያጠያይቅም፤ በተለይ አቶ መለስ የፈለጉትን ወንጀል ቢፈፅሙ ከድርጅቱ አባሎች ምንም ዓይነት ተቃውሞ መጠበቅ አይቻልም፡፡

እነ አቶ ስብሓት የቡድናቸውን አቋም የድርጅቱ አቋም በማስመሰል ሲናገሩ የደርጅቱ አባሎች ያልተወያዩበት እንደሆነ ቢታወቅም ድርጅቱ የአቶ ስብሓት አባባል ከእውነት ጋር እንደማይገናኝ ለመግለፅ የሚያስችል ነፃነት ያለው ሰው የለውም፡፡ አቶ ስብሓት የህወሓት ለኤርትራ ነፃነት መቆምን አስመልክተው ሲናገሩ ድርጅቱን የማያውቅ ሰው የህወሓት አባሎች ተወያይተው የኤርትራ ችግር በነፃነት ብቻ እንደሚፈታ አምነው የተቀበሉትና የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች መሰረታዊ ቅራኔ እንዳላቸው ስለዚህም በእኩልነት አብረው ሊኖሩ እንደማይችሉ የወሰኑ ሊሚስለው ይችላል፡፡ ምስጢሩ ግን ሌላ ነው፤ በህወሓት ውስጥ ለኤርትራ ችግር መፍትሄው ምን ቢሆን እንደሚሻል ውይይት ተደርጎበት አያውቅም፡፡

በህወሓት ውስጥ እንዲለመድ በተደረገው የመለስ ስታሊናዊ አሰራር መሰረት አንድ አባል በድርጅቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ የተደረገ ሃሳብን ለመቃወም ወይም በድርጅቱ ውስጥ ተነስቶ የማያውቅ አዲስ ሃሳብን ለመግለፅ ለማንም ሰው ከመናገሩ በፊት ካመራሩ ብፅሑፍ ፈቃድ መጠየቅ አለበት፡፡ ይህንን የውይይት ርእስ (አጀንዳ) ለማቅረብ ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ በመለሳዊ አባባል እንደ መብት በፅሑፍ ላይ ሰፍሯል (በትግርኛ፡ ህንፃ ማሌሊት፣ ሓምለ 1977፣ ገፅ 9)፡፡ የዚህ ግዴታ ዓላማ እነ መለስ ከሚፈልጉት ውጭ የሆነ ሃሳብ በድርጅቱ ውስጥ እንዳይሰራጭና ተቀባይነት እንዳያገኝ ማገድና የአንድነት፣ የዴሞክራሲና የፍትሕ ጥያቄዎች ማፈን ነው፡፡

አቶ ስብሓት የመንግሰታቸው የሽብር አገዛዝ በይፋ ለሚያውቀውና በዛ ለሚሰቃየው የኢትዮጵያ ህዝብ ስለ ዴሞክራሲ ሲያወሩለት ትእዝብቱ ለህዝቡ እንተወዋለን፡፡ "በህወሓት ውስጥ ለኤርትራ ችግር መፍትሄው ምን ቢሆን እንደሚሻል ውይይት ተደርጎበት አያውቅም፡፡" ስንል ግን ሰውየው "ለራሱ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚፈልግ ሰው የሌላውም መብት መቀበል አለበት፤" ስለዚህም ህወሓት ለኤርትራ ነፃነት መታገሉ የድርጅቱ ብስለት ያሳያል፡፡ ከሚሉት ጋር ይጋጫል፡፡ የድርጅታቸው አባሎች መብቶች የማያከብሩ አቶ ስብሓት ስለ መብት ማውራታቸው የለመዱት ቅንነት የጐደለው ዲስኩር ነው፡፡ እርግጥ የህወሓት አባሎች የኤርትራ ህዝብ መብት እንዲጠበቅ ይደግፉ ነበር፤ ይህ መብት ግን ኢትዮጵያንና ኤርትራን በመለያየትና በመለያየት ብቻ እንደሚረጋገጥ ደግፈው የሚያውቁበት ጊዜ አልነበረም፡፡

ኤርትራውያን ራሳቸው ህዝቡ የአንድነትን፣ የፌደረሽንና ኮንፌደረሽንን የመፍትሄ አማራጮች እንደነበሩት ባልዘጉበት ጊዜ እነ አቶ መለስ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ለነፃነት ብቻ ታግለዋል፣ ብዙ ፅፈዋል፣ ሰላማዊ መፍትሄ የሚፈልጉ ኤርትራውያንን

(ለምሳሌ ዶክተር ተስፋፅዮን መድሃንየን) በካሃዲነት አውግዘዋል፣ ሰድበዋል፡፡ አቶ ስብሓት በቃለ መጠይቃቸው ላይ ይህንን ፀረ አንድነትና አሳፋሪ ድርጊት እንደ ትልቅ ቁም ነገር አቅርበውታል፤ የኢትዮጵያ ህዝብን እንዳሳመኑበትም ገልፀዋል፡፡

የአቶ ስብሓት አገዛዝ በአዲስ አበባ በ1985 ዓ/ም የመጀመሪያውን የጅምላ ጭፍጨፋ የፈፀመው የኤርትራን መለየት በመቃወም ለሰላማዊ ሰልፍ በወጡ ተማሪዎች ላይ ነበር፡፡ እነ አቶ መለስ እንኳንና የኢትዮጵያ ህዝብን ሊያሳምኑ ብህወሓት/ማሌሊት ውስጥ በአንድ አጋጣሚ የተከሰተው አቋም ብንገልፅ አቶ ስብሓት የሚሉት ከእውነት የራቀ እንደሆነ በግልፅ የሳያል፡፡ አጋጣሚው በጀርመን አገር፣ በኮሎኝ ከተማ በ1979 ዓ/ም የተደረገ በአውሮፓ የህወሓት የብዙሃን ማህበር ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ የስብሰባው ተሳታፊዎች ብህወሓት ታጋዮች ውስጥ ተነስቶ የማያውቅ የውይይት ርእስ፣ የኤርትራ ህዝብ ችግር እንዴት ይፈታ? የሚል ጥያቄ አነሱ፡፡ በስብሰባው ላይ ሰባት የህወሓት ታጋዮችና በተደራቢ የማሌሊት አባሎች የነበሩ፣ ነበሩ፡፡ ከሰባቱ ሁለቱ፣ ስዩም መስፍንና አዲስአለም ባሌማ የአቶ መለስ አፈ ቀላጤዎች ስለነበሩ ለኤርትራ ነፃነት እንታገላለን ሲሉ አምስቱ ደግሞ የኤርትራውያንን መብት ልክ እንደ ኦሮሞ ህዝብ መብት እንደሚያከብሩና የህዝብ ውስኔ እንደሚቀበሉ ነገር ግን መለያየት እንሱ የሚፈልጉት ምርጫ እንዳልሆነ፣ ስለዚህ ህወሓት ይሁን የብዙሃን ማሕበሩ ለኤርትራ ነፃነት መታገል እንደሌለባቸው ገለፁ፡፡ ይህ አቋም በዛ አጋጣሚ ከተገኙት የህወሓት አባሎች ከ70% በላይ አንድነትን እንደሚፈልጉ አሳየ፡፡ ይህ አጋጣሚ የአቶ መለስና የአቶ ስብሓት ካድሬዎች ባሉበት አጠቃላይ የህወሓት ስብሰባ ቢጠራና ነፃ ውይይት ቢደረግ የህወሓት አባሎች በከፍተኛ ድምፅ አንድነትን እንደሚመርጡ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንግዲህ አቶ ስብሓት በህወሓት ውስጥ ለውይይት አቅርበዉት የማያውቁትንና የድርጅታቸው አባሎች አመቺ አጋጣሚ ሲያገኙ ህወሓት ከተቋቋመ ከ12 ዓመት በኋላም የተቃወሙትን አቋም የኢትዮጵያ ህዝብን በምንም ታምር ሊያሳምኑበት እንደማይችሉ ግልፅ ነው፤ በጉልበት ግን ጭነውበታል፡፡

የህወሓት ገዢዎች ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ለምን ፈለጉ? ለሚለው ጥያቄ አንዱ መልስ እነ አቶ መለስ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል በይፋ ካወጡት ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማ (የ1968 ማኒፌስቶ) ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው፡፡ እነሱ ራሳቸው ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ያልፈለጉ ሰዎች ትግራይን በሃሳባቸውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ከለዩ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆና እንድትቀጥል ሊፈልጉ አይችሉም፡፡

የመገንጠል ፍላጎት ህወሓትና የኤርትራ ድርጅቶች የሚጋሩት ስለዚህም የሚግባሉበት ስልጣን ስላስቀረ እንዲተጋገዙ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነበር፡፡ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ለተመሳሳይ ዓላማ የትጥቅ ትግል ባካሄዱ ድርጅቶች መካከል መጣላት እንጂ በእኩልነት መተጋገዝ አለመታየቱ የሚያመለክተውም ሁሉም ከአላማ በላይ ስልጣንን እንደሚያስቀድሙ ነው፡፡ አቶ ስብሓት የህወሓትና የሻዕቢያ መተጋገዝ እንደነበረ፤ የትኛው የትኛውን ምን ያህል እንደረዳ ለማበላለጥ ሳይሞክሩ ሚዛናዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ሰውየው ያልጨመሩት አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር ሁለቱ ባይተጋገዙ ሁለቱም ለስልጣን የሚበቁበት ሁኔታ አለመኖሩን ነው፡፡

እነ አቶ ስብሓት በህወሓት ሰራዊት መጠናከርና በደርግ መዳከም ምክንያት በኢትዮጵያ ደረጃ ስልጣን መያዝ የሚችሉበት ሁኔታ ሲመቻች የህወሓትና የሻዕቢያ

ግንኙነት ለየግላቸው ስልጣን ከመተጋገዝ አልፎ የህዝብ መቀራረብ እንዳይኖር ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ ህወሓት ደርግን ከስልጣን ለማስወገድ ተቃዋሚዎች የህብረት ግንባር እንዲመሰርቱ የይስሙላ ጥሪ ሲያቀርብ ሻዕቢያ ሶቬት ህብረትን "ሶሻል ኢምፐሪያሊስት" ስለማይል ወደ ግንባሩ መግባት እንደሌለበት ለማሳመን ብዙ ቅስቀሳ አደረገ፡፡ ሁለቱ በየቦታቸው ስልጣን ከያዙ በኋላም አቶ ታምራት ላይኔ ለፍርድ ቤት ባቀረቡት ፅሑፍ እንደገለፁት የሻዕቢያ ባለ ስልጣኖች በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ትስስር (ምናልባት በፌደረሽን ኮንፌደረሽን) እንዲኖር ለመነጋገር ሲፈልጉ አቶ መለስ ይቃወሙ ነበር፡፡ እንደዚሁም የአሜሪካ አዳራዳሪዎች የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ሲያነሱ አቶ መለስ እንዳልተቀበሉት አቶ ታምራት ላይኔ ጠቅሷል፡፡ ስለዚህ አቶ ስብሓት ከኤርትራ ድርጅቶች በላይ ለኤርትራ ነፃነት መታገላቸውን ሲገልፁ እውነት አላቸው፡ ይኸውም በፀረ ኢትዮጵያና በፀረ አንድነት የአቋም ግትርነት፣ ራሳቸው እንደገለፁት ከአረብ ሊግ በመወገን፣ ሻዕቢያ በኤርትራ ነፃነት ከፀና የፈለገውን እንዲወስድ በማድረግ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ኤርትራውያን በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር እንዲወድቁ በማመቻቸት፣ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን የመለያየትና የህብረት ጥቅሞችና ገዳቶች በሰከነ መንፈስ ሳይወያዩበትና በጥድፊያ ለኤርትራ ነፃነት እውቅና በመስጠት ነበር፡፡

እዚህ ላይ የስልጣንና ጥቅም ጥያቄ ይመጣል፡፡ እነ አቶ መለስ የኤርትራ መገንጠልን የፈለጉት ትግራይንም ለመገንጠል ስለፈለጉ ነበር ከተባለ፤ የትግራይን መገንጠል "ከተዉት" ለምን የኤርትራንም አልተዉትም? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሻዕቢያ ባለበት የኢትዮጵያ መንግስት አቶ መለስ ፍፁም ስለጣን መያዝ እንደማይችሉና ከፍፁም ስልጣን የሚገኙ ጥቀሞችን እንደሚያጡ ያውቃሉ፡፡ አቶ ሰብሓት "ህገ መንግስቱ ከተነካ የኢትዮጵያ ኣንድነት የሚባል የለም፡፡" እንዳሉት በግልፅ አነጋገር፣ ስልጣን ካጡ አሁንም በ68ቱ ማኒፌስቶ እንደገለፁት ኢትዮጵያን አይፈልጉም፡፡ አገሮች በሰላምም ይሁን በነውጥ ህገ መንግስት በተቀየረ ቁጥር እንደማይበታተኑ እየታወቀ፣ አቶ ስብሓት በእሳቸው የወጣ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ የመኖርና ያለመኖር ቅድመ-ሁኔታ አድርገው ሲያቀርቡት የግንዛቤ መዛባት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ካልገዟት እንደማይፈልጓት ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለስልጣንና ለጥቅም ብቻ እስከፈለጓት ድረስ ስልጣንና ጥቅም የሚጋራ ጠንካራ ድርጅት ያላት ኤርትራን አለመፈለጋቸው ግልፅ ያደርጋል፡፡

ለነገሩ እነ አቶ መለስ፣ እነሱ ያልተካተቱበት የሻዕቢያና ደርግ ድርድር በእርቅ እንዳይቋጭና ደርግ ሰራዊቱን ከኤርትራ ወደ ትግራይ እንዳያዘምት ትልቅ ስጋት ፈጥሮባቸው ነበር፡፡ ህወሓት ይኸን ስጋት ለመግታት ምን አደረገ? ውጤቱስ ምን ነበር? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ህወሓት ሻዕቢያን ለማዳከም ሁለት ሃሳቦች፣ ማለት የኤርትራ ነፃነትና በነፃ ኤርትራ መገንባት ያለበት ስርኣት አንስቶ የኤርትራ ህዝብ ሻዕቢያን መደገፉ ትቶ ሌላ "ዴሞክራሲያዊ" ድርጅት እንዲያቋቁም ለመቀስቀስ ሞከረ፡፡ በኤርትራ ነፃነት ላይ ከኤርትራውያን የበለጠ ኤርትራዊ መስሎ ከነፃነት የተለየ መፍትሄ የፈለጉትን ኤርትራውያን ብክህደት ፈረጀ፡፡ አቶ መለስ ስማቸው ሳይፅፉበት፣ (በህወሓት ውስጥ አንድ ፅሑፍ ሲወጣ የድርጅቱ ያቋም መግለጫ መስሎ አባሎች በማእከላዊነት ተገደው እንዲቀበሉትና ፀሓፊው በሃላፊነት እንዳይጠየቅ የደራሲው ስም አይጠቀስም ነበር) "የኤርትራ ጠመንጃ አፈሙዝ ወደ ታች አይደፋም" በሚል ርእስ በፃፉት የተንዛዛ የስድብ

መፅሓፍ አንድ ግለ ሰብ ቢሰድቡም ግለ ሰቡን እንደ መንደርደሪያ ተጠቀሙባቸው እንጂ ያነጣጠሩት በሻዕቢያ ላይ ነበር፡፡ አቶ መለስ ለኤርትራ ህዝብ ሊያስተላልፉት የፈለጉት መልእክትም፡ ሻዕቢያ ለኤርትራ ነፃነት እስከ ድል አይታገልም፣ በሶቬት ህብረት አማለጅነት ከደርግ ጋር ይታረቃል ነው፡፡ በዛው ላይ ግን አቶ መለስ ሻዕቢያ ከደርግ ጋር ባይታረቅ ታሳቢ አድርገው ሲቀጥሉ፣ ባይታረቅም ሻዕቢያ በነፃ ኤርትራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አይገነባም ሲሉ ምክንያታቸው እሳቸው እንደመሰረቱት ማሌሊት (በትግርኛ ማረክሰ-ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ) ማለትም በአልባኒያው ኢንቨር ሆጃ ሃሳብ ስለማይመራ መሆኑ አሻሚ አልነበረም፡፡

አሁን አቶ ስብሓት የኤርትራ ድርጅቶች የዴሞክራሲያዊ ስርአት ራዕይ እንዳልነበራቸው የሚገልፁት ያኔ ኤርትራዊያኑ እንደ ህወሓት ሆጃዊ አመራር ስላልነበራቸው በህወሓት/ማሌሊት የተወቀሱበት ነው፡፡ የአቶ መለስ መፍትሄ ሻዕቢያን በማርክሰ-ሌኒናዊ ማለት ሆጃዊ ድርጅት መተካት ነበር፡፡ ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ሁለት ነገሮች ተደረጉ፡፡ በአንድ በኩል ለተወሰኑ ኤርትራውን ማርክሰ-ሌኒናዊ ድርጅት እንዲመሰርቱ በህወሓት/ማሌሊት ገንዘብ ሲሰጣቸውና "ሳግም" ለሚባል ድርጅት እርዳታ ሲደረግ በሌላ በኩል ኤርትራውያንን በዚህ አላማ ዙሪያ ለማስለፍ ቅስቀሳ ተጀመረ፡፡ ውጤቱስ? ውጤቱ ባዶ ነበር፡፡ ኤርትራውያን እንኳንና የሻዕቢያ የጀብሃ ደጋፊዎችም ኤርትራ ውስጥ ሌላ ድርጅት እንዲመሰረት በህወሓት የሚደረገውን ቅስቀሳ አምርረው ተቃወሙት፤ ሳግም የተባለው ድርጅትም ኢትዮጵያ ውስጥ በሻዕቢያ ሲታደን እነ አቶ መለስ አልታገዱትም፡፡

ሻዕቢያ ከህወሓት ተለይቶ ከደርግ ጋር ከሚታረቅ እሱ ጠፍቶ በሌላ እንዲተካ በነ አቶ መለስ የተደረገው ውጤት-አልባ ጥረት ከጭንቀት የመነጨና "ሻዕቢያ መታረቁ አይቀርም" ከሚል የተሳሳተ ተስፋ የመቁረጥ ግምገማ ተነስቶ "በሌላ እንተካው" የሚል ተጨባጭ ሁኔታን ያላገናዘበ ውሳኔ ነበር፡፡ ሻዕቢያ ግን ያ ሁሉ ቅስቀሳ ሲደረግበት "ዝም ልንል ስለፈለግን ዝም ብለናል" ብሎ ዘጋ፤ ህወሓት ስለተቃወመው ሳይሆን የደርግ መዳከም ስላየ ደግሞ ከደርግ ጋር ድርድሩን አልቀጠለም፡፡ ሻዕቢያ የጣልያን ፈር ተከትሎ ህዝብን በመለያየት ፈንታ ከደርግ ጋር ተስማምቶ በኢትዮጵያዊነቱ ቢቀጥል ኖሮ አቶ ስብሓት እንደሚሉት ከሃዲ የሚያሰኘው አልነበረም፡፡ እርግጥ ዴሞክራሲን ከማስፈን አንፃር ሲታይ ከደርግ ይሁን ከሻዕቢያ መሰረታዊ ለውጥ የሚጠበቅ አልነበረም፤ ሆኖም የህዝብ ትግል በመገንጠልና ባለመገንጠል መሆኑ ቀርቶ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር እንዲሆን መንገድ ሊከፍት ይችል ነበር፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የእነ አቶ መለስ ፍልጎት ስለተሟላ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አዲስ የጭፍጨፋ ዙሮች እየተካሄዱ ናቸው፣ የውሸት ክሶች መደርደር (ለምሳሌ በስየና በቅንጅት ላይ) የኢህአዴግ ገዢዎች የማንነት መግለጫ ሆኖዋል፣ የባሰ ዘግናኝ ጦርነት ባጭር ጊዜ ውስጥ ያስር ሺዎች ህይወት ቀጥፏል፣ በእነ አቶ መለስ ፀረ አንድነት ፖለቲካ ምክንያትም ተጨማሪ የመከፋፈል አደጋ ባገሪቱ ላይ እያንዣበበ ነው፡፡

አቶ ስብሓት ስልጣንን የያዙት እሳቸው እንደሚሉት በአላማ ተቀባይነት ነው ወይስ እንደሚታወቀው በሰራዊትና በመሳሪያ? ለሚለው ጥያቄ ሰውየው አላማቸው ወሳኝነት እንደነበረው የማታለል ቅስቀሳ አድርገዋል፡፡ በህወሓት ውስጥ ለድርጅቱ ድል ወሳኝ ሚና የተጫወቱት ታጋዮች ወታደራዊ አመራር የሰጡትና በሰራዊቱ ውስጥ

የተዋደቁት አባሎች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ህወሓት ተቀባይነት እንዲያገኝ ለዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትና ለእርዳታ ልመና ለውጭ የሚቀርቡት "ማስታወቅያዎች" የድርጅቱ ወታደራዊ አቅምና ድሎች ነበሩ፡፡ አቶ መለስና አቶ ስብሓት ወታደራዊ አመራር በመስጠት ባይታሙም ቁልፍ የስልጣን ቦታ ይዘው የድርጅቱን ዓላማ ይወስኑ ስለነበር የዓላማው ድል አድራጊነት በመግለፅ ራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ከመሞከር ተቆጥበው አያወቁም፡፡ ዓላማው ማሌሊታዊ ስለሆነ ሳይንሳዊ እንደሆነም ላገር ቤት የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ብዙ ተብሎለታል፡፡

አንድ ህዝብ በዓላማ (አቶ ስብሓት "ተለዋጭ ፕሮግራም" በሚሉት) ድርጅቶችን መምረጡ ማረጋገጥ የሚቻለው ሰላም ሲኖርና ህዝቡን በጉልበት የሚያዋክቡ ታጣቂዎች በሌሉበት ሁኔታ ነው፡፡ ጦርነት ባለበት ሁኔታ አቅም ያለው ለጊዜውም ቢሆን ማሸነፉ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ቅኝ ገዢዎች የብዝበዛና ጭቆና አገዛዝ አንሰራፍተው ለመቶዎች አመታት የቆዩት ከሚገዟቸው ህዝቦች የተሻለ የቴክኖሎጂ አቅም ስለነበራቸው ነው፡፡ በመሰረቱ በተወሰነ አካባቢ፣ ለተወሰነ ጊዜ አንድ የተወሰነ ቡድን ጉልበት አግኝቶ ስልጣን መያዙ በዓለም ውስጥ በተደጋጋሚ የሚያጋጥም ክስተት ነው፡፡ በውጊያ ማሸነፍ ለውጊያ የሰለጠነ ሰራዊት፣ ልምድ፣ ችሎታ፣ አመቺ ሁኔታ ወዘተ… የሚያመጡት ነው፡፡ በአፍጋኒስታን የታሊባኖች በውጊያ ባጭር ጊዜ ውሰጥ ስልጣን መያዝ፣ የአሜሪካ ኢራቅን መውረር በአላማ ቅንነት የተገኙ ድሎች አይደሉም፡፡ አላማ ወሳኝ ቢሆን ኖሮ አቶ መለስና አቶ ስብሓት በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ስልጣን መጠጋትም አይገባቸውም ነበር፡፡

ሰላማዊ ህዝብ ሁልጊዜ በሰላም ለመኖር ሰለሚፈልግ ከታጣቂዎች፣ ከሽፍቶችም ቢሆን ራሱን ለመከላከል ዝግጁ አይደለም፡፡ ስለዚህ ማንም ሰራዊት ያልተደራጀና ያልታጠቀ ህዝብን (ህዝቡ መሮት አማራጭ አጥቶ እስኪነሳ ድረስ) መቆጣጠር ይችላል፡፡ የደርግና የነ መለስ አገዛዞች ያረመኔ አገዛዞች ናቸው፡፡ ደርግ በይፋ ሲገድል የህወሓት መሪዎች ደርግን እያወገዙ ጫካ ውስጥ በድብቅ ይገድሉ ነበር፤ አሁን ደግሞ ግድያዎቹን ሊደበቁ በማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ አገሩን ለመበታተን የሚፈልጉትን እነ መለስን በትክክል ሳያውቅ ደርግ እንዲጠፋለት የሚፈልግበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ደርግ ሰራዊቱን ሙያው በሌላቸው ካድሬዎች ሲያዝረከርክ፣ ነፃ የሚያስቡና እርስ በርሳቸው የሚተማመኑ መኰንኖች ደርግን ሲቃወሙ፣ የሶቬት ህብረት እርዳታ ሲቀርና ምእራባዊያን ደርግን ለመጣል ተቃዋሚዎቹን ሲያግዙ ደርግ ፈረሰ፤ ሰራዊቱም እነ መለስን እንደ ወገን ስላያቸውና ድብቅ አላማቸውን ስላልተገነዘበ፣ እንደ ቅኝ ገዢ በትንቢ ከነቤተሰቡ ለልመና እንደሚዳርጉት ስላልጠረጠረ ትጥቁን ጥሎ ውጊያውን አቆመ፡፡

በማጠቃለል ሲታይ አቶ ስብሓት በቃለ-ምልልሳቸው በሰጡት መግለጫ የድርጅታቸው ወታደራዊ ድል በዓላማ ቅንነት የተገኘ ለማስመሰል ከመሞከር አልፈው ይህንን ህዝብን ከፋፍሎ በመግዛት ዓላማ ላይ የተመሰረተው ህገ-መንግስትን የኢትዮጵያዊነት መግለጫ አድርገው አቅርበውታል፡፡ ይህ ህገ-መንግስት ከተነካም ኢትዮጵያ እንደምትበታተን አስፈራርተዋል፡፡ በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የአንድነት መርህ እንደሚያምኑ ቢገልፁም ለመርሁ በኤርትራ ላይ ምንም ቦታ ሳይሰጡት ለኤርትራ ነፃነት ከኤርትራ ድርጅቶች በላይ እንደታገሉ፣ በኤርትራ ነፃነት አለመፅናትም እንደ ክህደት እንደሚያዩት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር የትግራይ ነፃነት

እንደተያያዘ ለመግልፅ ስላልፈለጉ ራሳቸው ያወጡትን የመገንጠል ማኒፌስቶ ባጣጣሉበት አንደበት እንደገና ህገ-መንግስቱ ከተነካ "ትግራይ ይወጣል" ብለው አጠናክረውታል፡፡

አቶ ስብሓት ህወሓትና ህግደፍ በመተጋገዛቸው ምክንያት ሁለቱም ለስልጣን እንደበቁ ቢያውቁም፣ ህግደፍ እስካልተዳከመ ድረስ ከሩቁ እንጂ በጣም ከቀረበ ጥቅም እንደሚጋራቸው ስለሚያውቁ ለኤርትራ ነፃነት በጣም የሚቆረቆሩ ይመስላሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሌላ ሃይል ስልጣን ቢይዝ ኤርትራን የሚወር አስመስለው ለማስፈራራትም የኤርትራ ነፃነት ከተነካ አብረው እንደሚታገሉ በሌለ አደጋ ዝተዋል፡፡ ሰውየው ሲናገሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ስሜት እንደሚያቆስሉ ደንታ ያላቸው አይመስሉም፡፡

ባገራችን ኢትዮጵያ በተለይ ከ 66 አብዮት ወዲህ በቀጣይነት የቆየው ስልጣንንና ጥቅምን ለማጠቃለል ጉልበት የመጠቀም ፖለታካዊ ባህል ቆሞ ህዝብም ከፍርሃት ነፃ ሆኖ የሚፈልገውን ዓላማና ድርጅት መምረጥ የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ አገር አቀፍ የሆኑና የፖለቲካ ድርጅት መሳሪያ ያልሆኑ ተቋሞች፣ እንደ ፍርድ ቤት፣ ሰራዊት፣ ፖሊስ፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የብዙሃንና የሙያ ማህበሮች ወዘተ. ያስፈልጉናል፡፡ ፍትህ እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥና ተቋሞቹ ገለልተኛ እንዲሆኑ ብዙ ወንጀል ከፈፀሙትና የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን ካላቸው ከአቶ መለስና ግብረ አበሮቻቸው መላቀቅ አለብን፡፡ ከደርግ ጋር የሰሩም ይሁን ኢህአዴግን በማገልገል ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድርጊታቸው መወገዝ አለበት፤ ሆኖም ወንጀል የሚፈፅሙትን ከማይፈፅሙት በተጨባጭ ማስረጃ መለየት ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ አጋጣሚ አቶ ስየ አብርሃ በውሸት ተወንጅለው፣ እሳቸውን ለማጥቃት በዋስ ከእስር ቤት ውጭ የመቆየት መብት የሚከለክል ህግ ባስቸኳይ ወጥቶ፣ ለ6 ዓመታት ከታሰሩ በኋላ በመፈታታቸው ምክንያት የሚሰማንን ደስታ እንገልፃለን፡፡

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር

ሐምሌ 1999 ዓ.ም